# የታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ማብራሪያ ሰነድ

# THE GRAND ETHIOPIAN RENAISSANCE DAM BOND GUIDELINES

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ኤምባሲ - በርሊን

**2004 ዓ.ም.**

ቦንዱን በመግዛት በታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ግንባታ አሻራዎን ያኑሩ

**PURCHASE THE BOND AND PUT YOUR FINGER PRINT IN THE CONSTRUCTION OF THE GRAND ETHIOPIAN RENAISSANCE DAM ON THE ABAY RIVER**

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግስት በአባይ ወንዝ ላይ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ለመገንባት በቁርጠኝነት ተነሳስቷል:: ይህን ግንባታ ለማከናወን የሚያስፈልገው የፋይናንስ መጠን ከፍተኛ ሲሆን ገንዘቡንም ከሀገሪቱ ተወላጆችና ከአባይ ተፋሰስ አገሮች ዜጎች ለማሰባሰብ ታቅዷል:: በመሆኑም የሚፈለገውን ገንዘብ በቁጠባ መልክ ለማሰባሰብ እንዲቻል የህዳሴ ግድብ ቦንድ ለሽያጭ ቀርቧል:: የህዳሴ ግድብ ቦንድ በብር እና በሶስት ዋና ዋና የውጭ ገንዘቦች ማለትም በUSD, EURO እና በPound Sterling የተዘጋጀ ሲሆን ኤምባሲያችን ቦንዱን የሚሸጠው በዩሮ ነው:: በቦንድ ግዢ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑት በሀገር ውስጥ ያሉ መላ ኢትዮጵያውያን፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ ትውልድ ኢትዮጵያውያንና የአባይ ተፋሰስ አገሮች ዜጎች ሲሆኑ በዚህም ከቦንድ ግዢ ከሚያገኙት የወለድ ጠቀሜታ በተጨማሪ በታሪካዊው የህዳሴ ግድብ ግንባታ የራሳቸውን አሻራ እንዲያስቀምጡ ዕድል ይፈጥርላቸዋል::

## 2. የቦንድ ምንነት

ቦንድ እንደ ፕሮሚሰሪ ኖት ወይም የግምጃ ቤት ሰነድ የብድር (የዕዳ) ሰነድ ነው:: ከሌሎች የአጭር ጊዜ የብድር መንገዶችና ከግምጃ ቤት ሰነድ የሚለየው ለረጅም ጊዜ የሚያስገለግል በመሆኑ ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ ቦንድ ልክ እንደ ግምጃ ቤት ሰነድና እንደ ሌሎቹ የአጭር ጊዜ የክፍያ መሳሪያዎች ሁሉ በሁለተኛ ገበያ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ሊተላለፍ የሚችል፣ ተመልሶ ሊከፈል የሚችል፣ ወለድ ሊገኝበትና በአካልም ሆነ በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ አማካኝነት የሚሸጥ ነው::

## 3. የህዳሴ ግድብ ቦንድ ጠቀሜታዎች

### 3.1. ለአገር ያለው ጠቀሜታ

- ቁጠባን በማበረታታት እና ለኢንቬስትመንት በማዋል ለአገሪቱ ልማት መፋጠን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፣
- ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ካላቸው ገቢ በመቆጠብ ለሀገራቸው ልማት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ ለራሳቸው ተጠቅመው አገራቸውን እንዲጠቅሙ ያስችላቸዋል፣
- ኢንቬስትመንትን በማስፋፋት ተጨማሪ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፣
- የገንዘብና ፋይናንስ ገበያ እንዲስፋፋ ይረዳል፣


COMMERZBANK BERLIN: KNONTO NO. 209969500 BLZ: 100 400 00
SWFT: COBADEFF IBAN: DE22 1004 0000 0209 9695 00

3.2. ለገዢዎች ያለው ጠቀሜታ

- ቦንድ ገዥው ከገቢው በየጊዜው ገንዘብ እንዲቆጥብ በማድረግ ሀብት እንዲፈጥር ያደርገዋል፣
- የመንግስት ዋስትና ያለው በመሆኑ አስተማማኝ ሰነድ ነው፣
- ከቦንድ ግዥ የሚገኘው የወለድ ገቢ ከቀረጥ ነፃ ነው፣
- ቦንዱን ለገዢው ሕጋዊ ወራሾች እንዲሁም ለሌላ ሁለተኛ ወገን በውርስና በስጦታ ማስተላለፍ ይቻላል፣
- ቦንዱን በሁለተኛ ገበያ (secondary market) ለሌላ ሰው ወይንም ድርጅት መሸጥ ይቻላል፣
- እንዲሁም ቦንዱን በዋስትና አሲይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ገንዘብ መበደር ይቻላል::

## 4. የህዳሴ ቦንድ ባህሪያት

4.1. የቦንዱ ዓይነት

4.1.1 ወለድ የሚከፈልበት ኩፖን ቦንድ፣

4.1.2 ወለድ የማይከፈልበት ኩፖን ቦንድ፣

4.2 የቦንዱ ስያሜ: ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቦንድ፣

4.3 የቦንዱ ባለቤትና አቅራቢ: የኢትዮጵያ የኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን፣

4.4 የቦንዱ ወኪል ሻጮች: የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ወደፊት የሚወከሉ ሌሎች ድርጅቶች፣

4.5 ቦንዱ ለሽያጭ የሚቀርብባቸው ቦታዎች: በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኤምባሲዎች ወይም ቆንስላዎች ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤቶች እና ወደፊት የሚገለጹ ሌሎች ወኪሎች፣

4.6 ቦንዱ የሚከፈልበት ጊዜ: የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ፣

4.7 የቦንድ ወለድ የሚከፈለው: በየግማሽ ዓመቱ፣

4.8 ዋስትና: መንግሥት ለቦንዱ ሙሉ ዋስትና ሰጥቶታል፣

4.9 የገቢ ግብር: ከቦንዱ ግዢ የሚገኝ የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው::

4.10 የባንክ ብድር: ቦንዱን አስይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ብድር መውሰድ ይቻላል::


COMMERZBANK BERLIN: KNONTO NO. 209969500 BLZ: 100 400 00
SWFT: COBADEFF IBAN: DE22 1004 0000 0209 9695 00

**5. የቦንድ ዋጋ**

5.1 የቦንድ ዋጋ (bond value) በዶላር፣ ዩሮ እና ፓውንድ-ስተርሊንግ ባለ 500፣ 1000፣ 3000፣ 5000 እና 10000 ሲሆኑ የሕዳሴ ግድብ ታሪካዊ ከመሆኑና ሁሉም ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በቦንድ ግዢ ለመሳታፍ ያሳዩትን ተነሳሽነት ከግምት ውስጥ በማስገባት መንግስት አነስተኛ የቦንድ ሰነዶችን በባለ 50፣ 100 እና 300 ጭምር ለገበያ አቅርቧል::

5.2 በተጨማሪነት ቅንስናሾችን ለማስተናገድ እንዲቻል በዶላር፣ በዩሮ እና ፓውንድ ስተርሊንግ ባለ 5 እና 10 ዋጋ ያላቸው ቦንዶችም ለሽያጭ ቀርበዋል:: ለምሳሌ አንድ ግለሰብ የ55 ዶላር ቦንድ መግዛት ቢፈልግ አንድ ባለ 50 ዶላር ቦንድ እና ተጨማሪ ባለ 5 ዶላር ይሰጠዋል ማለት ነው::

**6. የቦንድ የክፍያ ጊዜ፣**

6.1 የቦንዱ ዝቅተኛ የክፍያ ጊዜ 5 ዓመት ሲሆን፣

6.2 ባለ 7 ዓመትና፣

6.3 ከፍተኛው ደግሞ ባለ 10 ዓመት ናቸው::

**7. የቦንዱ ወለድ፣**

7.1 ወለድ መታሰብ የሚጀምርበት ጊዜ: የቦንዱ ወለድ መታሰብ የሚጀምረው ቦንዱ ከተገዛበት ወይም የቦንዱ ግዢ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል::

7.2 የወለድ መጣኔ:

የሚከፈለው የወለድ መጣኔ የቦንዱን የክፍያ ጊዜ ያገናዘበ ሆኖ:-

- 5 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላለው .................. LIBOR + 1.25 በመቶ
- 7 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላለው ............ LIBOR + 1.5 በመቶ
- 10 ዓመት የክፍያ ጊዜ ላለው........... LIBOR + 2.0 በመቶ

*LIBOR, (London International Offer Rate) ማለት በለንደን የገንዘብ ገበያ ባንኮች በየዕለቱ እርስበርሳቸው የሚበዳደሩበት የወለድ ምጣኔ ነው:: ይህ ምጣኔ ብዙ ባንኮች የራሳቸው የወለድ ምጣኔ ለመወሰን እንደመነሻ የሚጠቀሙበት ነው:: የየዕለቱን የLIBOR ምጣኔን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድረ-ገጽ አድራሻ* **http://www.combanketh.com** *ላይ መመልከት ይቻላል::*


COMMERZBANK BERLIN: KNONTO NO. 209969500 BLZ: 100 400 00
SWFT: COBADEFF IBAN: DE22 1004 0000 0209 9695 00

### 7.3 የወለድ አጠቃቀም፡

የወለድ ክፍያ የሚፈጸመው የቦንዱ ግዢ የተፈፀመበትን የምንዛሪ ዓይነት መነሻ በማድረግ በዶላር፣ ፓውንድ ስተርሊንግ እና ዩሮ ሲሆን ገዢው ወለዱን፡-

- በግንባር በመቅረብ ወይም በሕጋዊ ወኪል በኩል መውሰድ፣
- ለሌላ ተጨማሪ ቦንድ ግዢ ማዋል፣
- በውጭ ምንዛሪ ወይም በብር በሚከፍተው ሒሳብ ገቢ ሊያደርግ፣
- ለተያዩ ክፍያዎች ሊጠቀሙበት ይችላል፡፡

## 8. ቦንድ ለመግዛት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች፣

8.1 ቦንድ የሚሸጠው ለኢትዮጵያዊያን፣ትውልድ ኢትዮጵያዊያንና ለአባይ ተፋሰስ አገሮች ዜጎች ነው፣

8.2 ኢትዮጵያዊያን ፓስፖርት በማቅረብ ቦንድ ግዥ መፈጸም ይችላሉ፣

8.3 ትውልድ ኢትዮጵያዊያን የውጭ ሀገር ዜጐች በተወላጅነት መታወቂያ የቦንድ ግዥ መፈጸም ይችላሉ፣

8.4 ከላይ በተራ ቁጥር 8.2 እና 8.3 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ማቅረብ የማይችሉ የኮሙዩኒቲ አባላት ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልድ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ሌሎች ማስረጃዎች በማቅረብ ቦንዱን መግዛት ይችላሉ፣

8.5 ከውጭ ምንዛሪ ሂሳባቸው ላይ የቦንድ ግዢ መፈጸም የሚፈልጉ ተወላጆች ከሂሳባቸው ወጪ በማድረግ ቦንድ መግዛት ይችላሉ፣

## 9. ቦንዱን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች

የክፍያውን ገንዘብ በኤምባሲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ፣ ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው በሚገኝ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤት በመቅረብ የቦንድ ግዢ መፈፀም ይቻላል፡፡ ኤምባሲ ተሂዶ ለሚፈፀም ማንኛውም የቦንድ ግዢ የመላኪያ ክፍያ አይጠየቅም፡፡ሂደቱም፣

- ገዥው ፓስፖርት/የተወላጅነት ማረጋገጫ መታወቂያ/ሁለቱን ማስረጃዎች ከሌለው ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልድ ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያሳዩ ሌሎች ማስረጃዎችን ይዞ ወደ ኤምባሲ በመቅረብ የማመልከቻ ቅጽ ይሞላል፣
- ገዢው ክፍያውን ለኤምባሲ ሲፈፅም ወዲያውኑ ቦንዱን ከኤምባሲው ያገኛል፡፡

## 10. የህዳሴ ቦንድን ለሁለተኛ ወገን ስለማስተላለፍ፤

10.1 ቦንዱን በውጭ ምንዛሬ ለሁለተኛ ወገን ማስተላለፍ የሚቻለው በውጭ ለሚኖር ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልድ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የውጭ ሀገር ዜጐች ነው፡፡ ነገር

ግን ቦንዱ በሀገር ውስጥ ገንዘብ እንዲከፈልለት ከፈለገ በሀገር ውስጥ ለሚኖር ኢትዮጵያዊ ማስተላለፍ ይችላል::

10.2 ገዢው ቦንዱን ለሁለተኛ ወገን በጀርባው ላይ በመፈረም ብቻ በውርስ እና በስጦታ ማስተላለፍ፣ ቦንዱን አስይዞ ከሀገር ውስጥ ባንክ ገንዘብ መበደር ወይም ቦንዱን በሁለተኛ ገበያ (secondary market) ለሌላ ግዢ መሸጥ ይችላል::

10.3 በእያንዳንዱ የቦንድ ኩፖን ጀርባ ላይ ቦንዱን እስከ ሶስት ሰው ድረስ ለማስተላለፍ የሚችልበት ቦታ እንዲኖር የተደረገ ቢሆንም ቦንዱን ከሶስት ሰው በላይ ማስተላለፍ ቢፈለግ በኤምባሲዎች ወይም ቆንስላዎች ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤቶች አስተላላፊውና የሚተላለፍለት ሰው በአካል በመቅረብ የቦንድ ማስተላለፊያ ቅጽ በመሙላት ማስተላለፍ ይቻላል::

10.4 ቦንዱ የተላለፈለት ግለሰብ ሲፈለግ የቁጠባ ሂሳብ ሊከፈትለት ይችላል::

## 11. የህዳሴ ቦንድ በሁለተኛ ወገን ስም ስለመግዛት፤

11.1 የህዳሴ ቦንድን ለሌላ ሰው መግዛት ይቻላል:: ነገር ግን ቦንዱ ላይ ስሙ የሚጻፈው ቦንዱ የሚገዛለት ሰው ስም /የቦንዱ ባለቤት/ መሆን አለበት:: በሌላ ሰው ስም ቦንዱን የሚገዛው ሰው በቦንዱ ላይ «ስለ» ብሎ መፈረም ይችላል:: በየጊዜው የወለድ ክፍያ የሚፈፀመውና ዋናው ገንዘብ ተመላሽ የሚደረገው ግን ቦንድ ለተገዛለት ሰው ወይም ህጋዊ ውክልና ለተሰጠው/ጣት ነው::

11.2 ለአቅመ አዳም/ሔዋን ላልደረሱ ልጆች በወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው አማካኝነት በቦንዱ ላይ የልጁን/ቷን ስም በመፃፍና «ስለ» ብለው በመፈረም ቦንዱን መግዛት ይችላሉ:: ልጁ/ቷ 18 ዓመት እስኪሞላው/ሞላት ድረስ ከቦንዱ የሚገኘው ጥቅም እንዲቀመጥ ወላጅ/አሳዳጊ ከፈለገ በዚሁ መሠረት ማስተናገድ ይቻላል::

## 12. የህዳሴ ቦንድ የሽያጭ ክንውን የተሳካ እና የተቀላጠፈ ለማድረግ በሁለተኛ ወገን ስም ስለመግዛት፤

በቦንድ ግዢ የተሰበሰበው የውጭ ምንዛሪን ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በበርሊን የኢፌዴሪ ኤምባሲ በ COMMERZBANK በተከፈተው የሂሳብ ቁጥር /KNONTO NO./ 209969500 መለያ ቁጥር /BLZ/ 100 400 00 SWFT: COBADEFF እና IBAN: DE22 1004 0000 0209 9695 00 ገቢ ይሆናል:: ኤምባሲው የመለኪያውን ወጪ ከራሱ በመሸፈን ገቢ የሆነውን ገንዘብ በህዳሴ ግድብ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተው አካውንት ገቢ ያደርጋል::

## 13. የህዳሴ ቦንድ የዋና ገንዘብ (principal) የክፍያ ሁኔታ፤

13.1 ቦንድ የገዛ ሰው የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ዋናውን ተመላሽ ገንዘብ:

13.1.1 በውጭ ምንዛሪ ሊወሰድ፣

13.1.2 በውጭ ምንዛሪ ወይም በብር በከፈተው/በሚከፍተው ሂሳብ ገቢ ሊያደርገው፣

13.1.3 ሌላ ተጨማሪ ቦንድ ሊገዛበት ወይም

13.1.4 ከውጭ ለሚገቡ ዕቃዎች ክፍያ ሊፈጽምበት ይችላል::

13.2 አንድ የተሸጠ ቦንድ የመመለሻው ጊዜ ከደረሰና ቦንዱን የገዛው ግለሰብ ወይም ድርጅት ሳይመጣ ቢቀር ገንዘቡ በስሙ ተይዞ ከቦንዱ የክፍያ ቀን በኋላ እስከ 10 አመት ድረስ ይቆያል:: ነገር ግን ከቦንዱ የመመለሻ ጊዜ (maturity date) በኋላ በቦንዱ ላይ ምንም ወለድ አይታሰብለትም::

13.3 የተሸጠ ቦንድ የመመለሻው ጊዜ ሲደርስ የጊዜ ገደቡን ማደስ/ማራዘም አይቻልም:: ነገር ግን ሌላ ቦንድ መግዛት ይቻላል::

13.4 ቦንድ የገዛ ሰው ቦንዱን ለሁለተኛ ወገን ሳያስተላልፍ ቢሞት ህጋዊ ወራሾቹ የወራሽነት ማስረጃ በማምጣት የቦንዱን ዋናውንና ከቦንዱ የሚገኘውን ጥቅም ማግኘት ይችላሉ:: ወራሹ በሀገር ውስጥ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ከሆነ ክፍያው የሚፈጸመው በብር ይሆናል::

## 14. በተለየ ሁኔታ የሚስተናገዱ ገጠመኞች:

14.1 የተገዛ ቦንድ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ፤

14.2 ቦንድ የጠፋበት/የተሰረቀበት ሰው በ24 ሰዓት ውስጥ ስለሁኔታው ፖሊስ ዘንድ ቀርቦ በማመልከት ማስረጃ መያዝ ይኖርበታል:: የመረጃውንም ኮፒ ለኤምባሲ፣ ቆንስላ ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ወይም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማቅረብ ማስመዝገብ ይኖርበታል::

14.3 ቦንዱ የተሰረቀበት ወይም የጠፋበት ግለሰብ ከፖሊስ ያገኘውን ማስረጃ ይዞ ኤምባሲው ዘንድ በመቅረብ ለጠፋው ቦንድ ምትክ ሌላ ማስረጃ /ሠርተፍኬት/ መውሰድ ይችላል::

14.4. ቦንድ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ቢበላሽ ለኤምባሲው፣ ቆንስላ ወይም ልዩ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ወይም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማሳወቅ እና የተበላሸውን ይዞ በመቅረብ በምትኩ ሌላ ማስረጃ /ሠርተፊኬት/ መውሰድ ይቻላል::

---------------------------- // ------------------------------

# የታሳቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ቦንድ ስመግዛት የቃል መግቢያ ቅጽ

1. ስም: ___________________________________

2. አድራሻ:___________________________________
   ___________________________________
   ___________________________________

3. ስልክ: ________________________________

4. ኢ-ሜይል: ________________________________

5. የሚገዙት የቦንድ መጠን (በዩሮ): ________________

6. የሚገዙት የቦንድ ዓይነት (ምርጫዎን የ'X' ምልክት በሳጥኑ ውስጥ በማስቀመጥ ይግለጹ):
   - ባለ 5 ዓመት .................. LIBOR + 1.25 በመቶ ☐
   - ባለ 7 ዓመት .................. LIBOR + 1.5 በመቶ ☐
   - ባለ 10 ዓመት ............... LIBOR + 2.0 በመቶ ☐

እኔ ______________________________ በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባውን የህዳሴ ግድብ ቦንድ በመግዛት የሀገሬን ልማት ለመደገፍ ሙሉ ፍላጎትና ዝግጁነት ያለኝ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

ፊርማ _______________________

ቀን _________________________

- **ቦንድ በመግዛት የህዳሴውን ግድብ በጋራ ዕውን እናድርግ!**
- **ሀገራችንን ለማልማት እጅ ለእጅ ተያይዘን እንነሳ!**


COMMERZBANK BERLIN: KNONTO NO. 209969500 BLZ: 100 400 00
SWFT: COBADEFF IBAN: DE22 1004 0000 0209 9695 00